# 15th Ave S የማሻሻያዎች ፕሮጀክት

## የመንገዶችና የመንገድ ዳር እግረኛ መሄጃዎች ላይ የሚሠራው ስራ በቅርብ ይጀምራል።

በዚህ ሰመር (በጋ)፥ በአከባቢዎ በ15th Ave S ማሻሻያዎች ፕሮጀክት ላይ የሚሠሩት ቡድኖች ስራ ይበዛባቸዋል። ይህንን ስራ በፍጥነት፥ ሳይረብሽ እና ደህንነትን በጠበቀ መልኩ ለማጠናቀቅ ቡድኖቹ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋሉ። የግንባታ የጊዜ ሠሌዳዎች ሊለወጡ  ይችላሉ፥ ለአዳድስ መረጃዎች የፕሮጀክቱን ድረ-ገፅ ይመልከቱ: seattle.gov/transportation/15th-Ave-S-AAC.

የተወሰኑ የግንባታ በታዎች በካርታ ላይ የተመላከቱ ሲሆን እነዚህን ይጨምራል፡

- **በዚህ  የፀደይ ወቅት የፍሳሽ ማስወገጃ ስራ፥** የመንገድ ዳር እግረኛ መሄጃዎች እና የከርብ ማሻሻዎች፥ እንደዚሁም የመንገድ ጥገና ኤስ ስፖካን ጎዳና(S Spokane St)  እና  ኤስ ኮሎምብያን መንገድ (S Columbian Way)የሚገናኙበት በታ

- **በሰኔ አጋማሽ ጀምሮ፡ የፍሳሽ ማስወገጃ ስራ፥** የመንገድ ዳር እግረኛ መሄጃዎች እና የከርብ ማሻሻዎች፥ እንደዚሁም ደግሞ ኤስ ስፖካን ጎዳናን (S Spokane St )ይዞ ባሉት የመንገዶች ጥገና

  ከምህራብ ጀምሮ፥ ቡድኖቹ ፥ 15th Ave  S፥  16th Ave S፥ 17th Ave S፥ Alamo Pl S፥ እና 18th Ave S ጋር በሚገናኙበት መገናኛዎች ላይ ያተኩራሉ።

- **በተቻለ መጠን እስከ ሰኔ መጨረሻ፡** ኤስ ስፖካን ጎዳና ተከትሎ የአስፓልት ንጣፍ መሰባበር

  ይህ ስራ፥ በዚህ ዓመት መጨረሻ ለሚሰራው አስፓልት ስራ መንገዱን ለማዘጋጀት፥ ቢያንስ ለአንድ ሳምንት በምሽት ሰዓታት ይካሄዳል።

- **ከሰመርበጋ) አጋማሽ ጀምሮ፡** የማፍረስ፥ የኮንክርት ስራ፥ እና ኤስ ስፖካን ጎዳናና የቢኮን አቬን ኤስ ላይ የከባድ ጎርፍ ፈሳሽ ማስወገጃ ማሳደግ

  በትራፍክ ፊሰት ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ፥ የተወሰኑ ስራዎች በምሽትና የሳምንት መጨረሻዎች

  ላይ መሰራት አለባቸው።




### በግንባታው ወቅት ምን መጠበቅ እንዳለበት

የምሽት ወይም የሳምንት መጨረሻ ስራ ቢያስፈልግም እንኳ፥ የተለመዱ የስራ ሰዓቶች ከሰኞ እስከ ዐርብ ባሉት ቀናት ከ6 AM እስከ 6 PM ነው። የግንባታው ተፅዕኖዎች የሚያካትተው፡

- የመንገድ ዳርቻዎች ባሉት መስመሮች በጊዜያዊነት መዘጋት፥ ወዴ ኤስ ስፖካን ጎዳና የሚወስደውን መገደብ
- በዋና መገናኛዎች ላይ በሳምንት መጨረሻ መዘጋት
- የሚረብሹ ድምፆችና መንቀጥቀጥ (በተወሰኑ አጋጣሚዎች፥ ስራው የተቀመጠውን የተለመደ ከሚረብሽ ድምፅ ገደብ በማለፍ ስራው እንዲሰራ ለማስቻል የሲያትል ከተማ ጊዜያዊ የድምፅ መለዋወጥን ሊፈቅድ ይችላል።
- አቧራና ስብርባሪዎች
- ማቋረጫዎችና የመንገድ ዳር እግረኛ መሄጃዎች መዘጋት፥ እና በእግር ለሚሄዱትና ብሽክሌት ለሚያሽከረክሩት ሰዎች መገንጠያዎች
- የመስመርና መገንጠያዎች ለአሽከርካሪዎች መዘጋት
- በስራው አከባቢዎች የግንባት ስራና የመኪና ማቆሚያ ተፅኖዎች
- የአውቶብስ ማቆሚያ መቀላቀል ወይም ጊዜያዊ መዘጋቶች
- የውስጥ ለውስጥ መንገድ መዘጋቶች (ነዋሪዎች አስቀድመው እንዲያውቁ ይደረጋል)

### የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ሁኔታ/ ገፅታ

15th Ave S በኤስ ስፖካን ጎዳና እና አንጀሊን ጎዳና መካከል ወዴ ቢኮን ሂል የሚሄዱና በዚያ ለሚያለፉ ሰዎች አስፈላጊ መገናኝን ይፈጥራል። ማንኛውም ሰው በሠላምና በምቹ ሁኔታ ወደ ሚፈልጉት መሄድ እንዲችሉ፥ SDOT የሁሉንም ተጠቃሚዎች ፍላጎት ባመጣጠነ መልኩ በዚህ ኮርዶር ላይ ማሻሻያ እያደረገ ይገኛል።

### ይከታተሉን

ሊኖር ስለሚችል የመንገድ መዘጋቶችን፥ መገንጠያዎች፥ እና የስራ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ በየጊዜው መረጃ ለማግኘት ተመራጩ መንገድ

የፕሮጀክታችን ድረ-ገፅ መጎብኘትና ለኢሜልና ለፅሑፍ ማስታወቂያ ደግሞ መመዝገብ፡

የተተሮገመ መረጃ በድህረ-ገፃችን ላይ ይገኛል።

*Have more questions? Interested in receiving project updates?*

**VISIT:** seattle.gov/transportation/15th-Ave-S-AAC

**EMAIL:** 15thAveAAC@seattle.gov    **PHONE:** (206) 775-8719

Seattle Department of Transportation

The Levy to MOVE SEATTLE